# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 226 መስከረም 3 2005 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ራዕይ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቱ የተከበረበት፤ የኢኮኖሚ ብልፅግናና ማኅበራዊ ፍትህ የሚገኝበት፤ የዜጎች ሕይወት፣ ደህንነትና ጥቅም የተከበረበት እና የሕዝቧ አንድነትና ትስስር የጠነከረበት ሃገር እንዲኖረው ማድረግ ነው።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የቀድሞ የህወሃት አመራር አባላት ወደሥልጣን ለመመለስ ከፍተኛ ተጋድሎ እያደረጉ መሆኑን ምንጮች አጋለጡ

የጸረ ደርግ ትግል አሸንፈው ሥልጣን ከተቆጣጠሩ ቦኋላ በሂደት ከአመራር አባልነታቸው መተካካት በሚለው የመለስ ዜናዊ ፖሊሲ ከነበሩበት ሃላፊነት ተገልለው የነበሩ የቀድሞ የህወሃት አመራሮች የመለስ ዜናዊን ከዚህ አለም በሞት መለየት ተከትሎ ድርጅታቸው የአመራር ክፍተት ገጥሞታል በሚል የከረረ ክርክር ወደ ሥልጣን ለመመለስ ሁኔታዎችን እያመቻቹ መሆኑን ለድርጅቱ ቅርበት ያላቸው የግንቦት 7 ምንጮች አጋለጡ።

እንደምንጮቻችን መረጃ እነዚህ አሁን ወደ ሥልጣን ለመመለስ መንገዳቸውን እያመቻቹ ያሉት የቀድሞ የህወሃት መሥራቾችና የረጅም ጊዜ አመራር አባላት የትግል ጓዳቸው መለስ ዜናዊ ከፉኛ ታሞ ለህክምና ወደ ቤልጂዬም ተወስዶ በነበረበት ወቅት ለረጅም ጊዜ ምስጥሩ እንዳይነገራቸው ተደርጎ የነበረ ከመሆኑም በላይ በውጪ አገር በሚገኙ ሚዲያዎች ዜናው ከተናፈሰ ቦኋላም ቢሆን ህመሙ ለከፉ እንደማይዳርገው ይነገራቸው እንደነበር ይህም ሆን ተብሎ ህወሃትን ለማዳከም የተደረገ ጥረት አካል ነው ብለው እያማረሩ እንደሆነ ታውቋል።

ህወሃትን ለድል በማብቃታቸው ብቻ ሳይሆን የተገኘውን ድል እስከወዲያኛው ከእጃቸው ላለማውጣት ቃልኪዳን የተገባቡት እነዚህ የቀድሞ አመራር አባላት አውራቸው የነበረው መለስ ዜናዊ ከሥራ ገበታው ላይ ከጠፋ ከሁለት ወራት ቦኋላ ሰለመጪው የህወሃት ዕድል ፋንታ በአቦይ ስብሃት አማካይነት እየተገናኙ መወያየት ጀምረው እንደነበር ቀደም ሲል መዘገቡ ይታወሳል።

በኢትዮ ኤርትራ ግጭት ወቅት ህወሃት ለሁለት ከተከፈለ ቦኋላ ከድርጅቱ ከተባረሩ የቀድሞ የህወሃት አባላትም አንዳንዶቹ አቦ ስብሃት አያሰባስቡዋቸው ካሉ ነባር አባላት ጋር የምስጥር ግንኙነት እንደጀመሩ ምንጮች ይናገራሉ።

መለስ ዜናዊ ህወሃትን ገድሎ ነው የሞተው የሚል ስሞታ ማሰማት እንደጀመሩ የሚነገርላቸው ነባር የህወሃት አባላት የመከላኪያ ሠራዊቱ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ከኦጋዴን ነጻነት ግንባር ጋር ድርድር መጀመሩን ባስታወቀ ማግሥት በክልሉ የሚኖሩ በርካታ ንጹሃን መጨፍጨፉ ይፋ ሆነ

መለስ ዜናዊ በህይወት በነበረበት ወቅት ወደ ኦጋዴን ክልል ያሰማራው የወያኔ ሰራዊት በክልሉ በሚኖሩ ንጹሃን ዜጎች ላይ የሚፈጽመውን ጭፍጨፋ እንደቀጠለበት በትናንትናው ዕለት ይፋ የሆነው መረጃ አጋልጦአል።

ይህ ሰሞኑን የተፈጸመው ጭፍጨፋ የወያኔ ኮሚኒኬሽን መሥሪያቤት ከኦጋዴን ብሄራዊ ነጻነት ንቅናቄ ጋር ኬንያ ውስጥ ድርድር ማድረጉን ይፋ ባደረገበት በመጀመሪያው ሳምንት ላይ መሆኑ የድርድሩን እውነተኝነት ጥያቄ ውስጥ ከቶታል ተብሎአል።

ቀደም ሲል በመለስ ዜናዊ ትእዛዝ በምስራቅ ኢትዮጵያ በሚኖሩ የኢትዮጵያዊያን ሶማሌዎች ላይ ሲፈጸም የነበረው ጥቃት የመለስ ዜናዊን ህልፈት ተከትሎ ጋብ ሊል ይችላል ተብሎ ታስቦ የነበረ ቢሆንም የመለስ ዜናዊን የተሳሳተ ፖሊሲ እንዳለ ይዘን እንቀጥላለን በሚሉት አምላኪዎቹ ት ዕዛዝ ጥቃቱ ተጠናክሮ መቀጠሉ ገሃድ እየሆነ ነው።

አዲሱ ጥቃት የተካሄደው ጳጉሜ 1 ቀን 2004 ዓ.ም በቆራሌ ቀበሌ ነው። በዚህ ጥቃት በርካቶች ሲገደሉ ቁጥራቸው በውል ያልተረጋገጠ ደግሞ የደረሱበት ጠፍቷል - እንደ አካባቢው ዓይን እማኞች።

በዚህ የግፍ እርምጃ ህይወታቸውን ማጣታቸው ከተረጋገጠው ውስጥ ፋይሳል ኢርሻድ፣ መውሊድ ሃሰን፣ ሞሃመድ ጉሌድ፣ ሲረር አብዱ፣ ፋራህ አሊ ኢጋሶ ማሊን፣ ቀዳር አህመድና ልጁ እንዲሁም ሌሎች አስር የአካባቢው ነዋሪዎች ይገኙበታል።

በዘረኛው የወያኔ ስርዓት የሚደርስበትን በደልና ግፍ እምቢ አልቀበልም ሲል በኖረው የቆራሌ አካባቢ ነዋሪ ላይ የወያኔ ሰራዊት በቅርቡ ጥቃት ሲሰነዝር የአሁኑ ለሁለተኛ ጊዜ ነው።

ግዜ ግንቦት 7 ዜና




## በወያኔ እስር ቤት ሲማቅቁ የነበሩ ሁለቱ ሲውዲናዊያን ጋዘጠኞች የተፈጸመባቸውን ሰቆቃ በማጋለጥ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጡ

በወያኔ ፍርድ ቤት የአሥራ አንድ አመት እስራት ተፈርዶባቸው ከአንድ አመት በላይ በቃሊቲ እስር ቤት ሲማቅቁ የቆዩት ሁለቱ ስዊዲናዊያን ጋዜጠኞች ማርቲን ሽበየ እና ጆን ፐርሰን በይቅርታ ሥም ተፈተው አገራቸው ምድር በደረሱ የመጀመሪያው ቀን ላይ በስቶክሆልም ሲውዲን ተሰብስቦ ይጠባበቃቸው ለነበሩ የአገሩ ጋዜጠኞች መግለጫ መስጠታቸውን የግንቦት 7 ተባባሪ ዘጋቢ ከስቶክሆለም በላከልን ዘገባ ገለጸ።

ሁለቱ ጋዜጠኞች አዳራሹን ሞልቶ ይጠባበቃቸው ለነበሩ ጋዜጠኞች ለእስር የዳረጋቸውንና እስር ላይ በነበሩበት ወቅት የተፈጸመባቸውን ሰቆቃ ለመግለጽ ወደ አዳራሹ ሲገቡ ደማቅና በጋለ ጭብጨባ የታጀበ የጀግና አቀባበል ነው የተደረገላቸው እንደተባባሪ ዘጋቢያችን ሪፖርት።

የወያኔ አገዛዝ በኦጋዴን ንጹሃን ዜጎቻችን ላይ የሚፈጽመውን የጅምላ ጭፍጨፋ ለመዘገብ ሱማሊያን አቋርጠው ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ እንደተያዙ በጋዜጣዊ መግለጫቸው ወቅት የተናገሩት ጋዜኛ ማርቲን ሽበየና ጋዜጠኛ ጆን ፐርሰን በቁጥጥር ሥር ባዋሉዋቸው የወያኔ ሰራዊት ከፉኛ ድብደባ እንደተፈጸመባቸውና በዚህም ድብደባ ምክንያት ብዙ ደም እንደፈሰሳቸው እንኳ እየተናነቃቸው ገልጸዋል።

ሁለቱም ጋዜጠኞች ድብደባው የተፈጸመባቸው ድንበሩን አቋርጠው እንደተያዙ በህይወት ዘመናቸው የማይተዋወቁትን ጥይት የጎረሰ የጦር መሳሪያ ይዘው ሲተኩሱ ፊልም እንዲቀረጹ የተሰጣቸውን ት ዕዛዝ ለመተግበር በማቅማማታቸው እንደሆነ ገልጸዋል። ድብደባውን (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የዘረኛው አገዛዝ ቁንጮ የነበረው መለስ ዜናዊ በሞት ቢለይም ህወሃት በወታደራዊ አዛዥነት ቦታ ላይ በብርጋዴር ጄኔራልነት ካሰሾማቸው 34 ወታደራዊ መኮንኖች 23ቱ የትግራይ ተወላጆች መሆናቸው ታወቀ

የኢትዮጵያ መከላኪያ ሠራዊት ውስጥ ካሉት 62 የአዛዥነት ቦታዎች 58ቱን በትግራይ ተወላጆች ተቆጣጥሮ ያለው የዘረኛው የወያኔ አገዛዝ፤ የአገዛዙ ቁንጮ የነበረው መለስ ዜናዊ ቀብር በተፈጸመ በሳምንት ዕድሜ ውስጥ ከኮሌኔርነት ማዕረግ ወደ ብርጋዴር ጄኔራልነት ማዕረግ ካሳደጋቸው 34 ወታደራዊ መኮንኖች 22ቱ፤ ከብርጋዴር ጀነራልነት ወደ ሜጀር ጄኔራልነት ካደጉ 3 መኮንኖች 3ቱም በድምሩ ከ37 ተሿሚዎች 25 ቱ የትግራይ ተወላጆች መሆናቸውን ቅርበት ያላቸው ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን በላኩት መረጃ አጋለጡ።

በወያኔ ምክትል ጠቅላይ ምንስቴር ሃይለማሪያም ደሳለኝ አቅራቢነት በጤና ችግር ምክንያት የአእምሮ ብቃታቸው እያነጋገረ ያለው የይስሙላው ፕሬዝዳንት ግርማ ወልደጊዮርጊስ ሹመቱን እንዳጸደቁት በወያኔ ቁጥጥር ሥር ባሉ መገናኛ ብዙሃን የተገለጸው የእነዚህ 34 ብርጋዴር ጄኔራሎችና ከብርጋዴር ጄኔራልነት ወደ ሜጀር ጄኔራልነት ያደጉ 3 ሰዎች ስም ዝርዝር ከምንጮቻችን በደረሰን የብሄረሰብ ማንነታቸው መሰረት የሚከተሉት ናቸው።

ከኮሎኔልነት ወደ ብርጋዴር ጄነራልነት የተሾሙት 34ቱ መኮንኖች በስማቸውና በብሔር ተዋጽኦዋቸው (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## መልካም አዲስ ዓመት ከብሩህ ራዕይ ጋር!!!

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን ከዘመን ወደ ዘመን አሸጋገረን ይላል። መጪው ዓመት ከወያኔ ዘረኛ ፖሊሲ ተላቀን ኢትዮጵያዊያን በአገራችን ጉዳይ ላይ ወሳኞች የምንሆንበት ዓመት እንዲሆን ይመኛል። በተጨማሪም አዲሱ ዓመት ኢትዮጵያዊያን የወያኔ ባለሟሎች በዘረፋ መከበርን እየታዘቡ መቆጨታቸው የሚያበቃበት፤ ሕዝብ የአገሩም የሃብቱም ባለቤት የሚሆንበት ሥርዓት መሠረት የሚጣልበት ዓመት እንዲሆን ይመኛል።

ያለፈው 2004 ዓ. ም. ግዙፍ የሆኑ አገራዊ ክስተቶች የሞሉት ዓመት ነበር። በፀረ ሽብርተኝነት ህግ ሽፋን በበርካታ ንፁሃን ዜጎች ላይ በደል ተፈጽሟል። የበደሉ ብዛት መምህር የኔሰው ገብሬን የመሳሰሉ ወጣቶች በገዛ ራሳቸው ሕይወት ላይ ሳይቀር እንዲፈርዱ አድርጓቸዋል። እጅግ የከፋ የኑሮ ውድነት በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎችን ወደ ስደት ገፍቷቸዋል። በጉራ ፈርዳ፣ ሲዳማ፣ ጋምቤላ፣ አፋር፣ ኦጋዴን፣ ወልቃይት ዋልድባ እና ሌሎችም የኢትዮጵያ ገጠሮች ኢትዮጵያዊያን አርሶ አደሮች ሲያለቅሱና ሲያነቡ ነው ዓመቱን ያሳለፉት።

በ 2004 ሙስሊምም ክርስቲያንም ወገኖቻችን የእምነት መብታቸውን ለማስከበር ትግል ውስጥ የገቡበት ዓመት ነበር። ሙስሊሞች ወያኔ በሃይማኖታቸው ጣልቃ እንዳይገባ ለመጠየቅና መሪዎቻቸውን በነፃነት ለመምረጥ፤ ክርስቲያኖች ደግሞ ዋልድባን ከጥፋት ለማዳን በሚያደርጉት ጥረት አብረው የቆሙበት ዓመት መሆኑ 2004 ዓ.ም. በበጎ የሚዘከርበት ሆኗል። ከሙስሊሞችና ክርስቲያኖች በተጨማሪም የኢትዮጵያ መምህራን የኑሮ ውድነትን ያላገናዘበ የይስሙላ የደመወዝ ጭማሪ በመቃወም የሥራ ማቆም አድማ የመቱበት ዓመት መሆኑ የወያኔ የአገዛዝ እድሜ እያጠረ መሆኑን ያመላከተ ዓመት ሆኖ አልፏል።

2004 ዓ. ም. የተጠናቀቀው በሁለቱ ዋና ዋና የሥርዓቱ ቁንጮዎች ማለትም በዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ እና በፓትሪያርኩ አቡነ ጳውሎስ ህልፈት ነው። ሁለቱም በተፈጥሮ ምክንያቶች በአንድ ወቅት ማለፋቸው ቤተመንግሥትም ቤተክህነትም አዲሱን ዓመት ከብዙ ብዥታዎችና ስጋቶች ጋር እንዲቀበሉ አስገድዷቸዋል።

የሟቹ የመለስ ዜናዊ ተከታዮች መጪዎቹ ዓመታት የጌታቸው ራዕም ተግባራዊ የሚደረግባቸው ዓመታት ናቸው ሲሉ ይደመጣሉ። ለመሆኑ የመለስ ዜናዊ ራዕይ ምን ነበር?

የመለስ ዜናዊ ራዕይ ኢትዮጵያን ከፋፍሎ ማዳከም፤ ዘረኝነትን ማንገስ፤ ሃብቷን መመዝበርና ማስመዝበር ነበር። ይህንን ራዕይ ለማሳካት ሲል ነው በቅድሚያ ህወሓትን ቀጥሎ በየቦታው አምሳያችን እና ኢህአዴግን ያደራጀው።

መለስ ዜናዊ በተወሰነ መጠን ራዕዩ ተሳክቶለት ኢትዮጵያን ከፋፍሎ አዳክሟል፤ የራሱን ጠባብ ቡድን አባላትንና ምስለኔዎቹን በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ መጠን ያለው ሃብት እንዲያካብቱ ረድቷቸዋል። ዛሬ እነሱ ማመን በማይቻል መጠን ከብረዋል። ተከባብሮ ይኖር የነበረው የኢትዮጵያ ሕዝብ እርስ በርሱ እንዲናቆር ተደርጓል። የመለስ ዜናዊ ባለሟሎች እንዲቀጥል የሚፈልጉት ይህ ነው።

የመለስ ዜናዊ ራዕይ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊያን መጥፊያ ነው። የመለስ ዜናዊ ራዕይ በዘራቸው የተመረጡ ጥቂት ሰዎች የተንቀባረረ ሕይወት ሲመሩ እያየ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በረሃብ እንዲያልቅ በችግር እየማቀቀ የምድር ሲኦል እንዲገፋ እየተደረገ ነው። የመለስ ዜናዊ ራዕይ ለም መሬታችን በሙሉ ለቻይና፣ ህንድና አረብ ቱጃሮች ተሰጥቶ ኢትዮጵያዊ ድሃ ገበሬ በስደት እንዲያልቅ፤ በገዛ ሀገሩ ባይትዋር እንዲሆን፤ የበይ ተመልካችና ተመጽዋች የሚያድርግ ነው። የመለስ ዜናዊ ራዕይ በቀበሌ ጀምሮ እስከ ፌደራል መንግሥት ያሉት የመንግሥት ሥልጣኖች በሙሉ በእሱ ወገኖች እጅ ውስጥ ሆኖ የፈለጉትን እያስቀመጡ ያልፈለጉትን ደግሞ እያነሱ እድሜ ልካችንን እንዲገዙን ነው። የመለስ ዜናዊ ራዕይ የኢትዮጵያ ጠላት ራዕይ ነው።

ስለሆነም የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ የመለስ ዜናዊ ተከታዮች የጌታቸውን ራዕይ የሚያሳኩበት እድል ሊሰጣቸው አይገባም።

በአንፃሩ የግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ራዕይ የሚከተለው ነው።

> *የግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ራዕይ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቱ የተከበረበት፤ የኢኮኖሚ ብልፅግናና ማኅበራዊ ፍትህ የሚገኝበት፤ የዜጎች ሕይወት፣ ደህንነትና ጥቅም የተከበረበት እና የሕዝቧ አንድነትና ትስስር የጠነከረበት ሃገር እንዲኖረው ማድረግ ነው።*

አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የግንቦት 7ን ራዕይ ይጋራል ብለን በጽኑ እናምናለን። የግንቦት 7 ራዕይ እውን እንዲሆን ግን የዚህ ራዕይ እንቅፋት የሆነው ወያኔ መገደድ አሊያም መወገድ ይኖርበታል።

አዲሱ 2005 ዓ. ም. ወያኔን አስገድደን ወይም አስወግደን ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች የተከበበሩባት፤ የኢኮኖሚ ብልፅግናና ማኅበራዊ ፍትህ የሚገኙባት፤ የዜጎች ሕይወት፣ ደህንነትና ጥቅም የተከበሩባት እና የሕዝቧ አንድነትና ትስስር የጠነከሩባት ሃገር መገንባት የምንጀምርበት ብርሃናዊ ዓመት እንዲሆንልን እንመኛለን።

**መልካም አዲስ ዓመት!!!**

................................................................................................................................................

## በወያነ እስር ቤት ሲማቅቁ የነበሩ ሁለቱ ሲውዲናዊያን ጋዘጠኞች የተፈጸመባቸውን ሰቆቃ በማጋለጥ

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የፈጸሙባቸው የመከላኪያ ሠራዊት አባላት የተሰጣቸውን ጠመንጃ ይዘው ፊልሙን የማይቀረጹና ጥፋተኞች ነን በማለት የምስክርነት ቃል የማይሰጡ ከሆነ በታጠቁት መሳሪያ እዚያው እንደሚገድሉዋቸው እንደዛቱባቸው እነርሱም በተፈጸመባቸው ማስፈራራት ተገደው ጥፋተኛ ነን ለማለት እንደቻሉና ወደ ኋላ ፍርድ ቤት ሲደርሱ ማስረጃ ሆኖ የቀረበባቸውን ቪዲዮ ተገደው እንደተቀረጹ አጋልጠዋል።

በትናትናው ዕለት መስከረም 4 ቀን ስቶክሆለም ውስጥ ጋዜጣዊ መግለጫውን የሰጡት ሁለቱም ጋዜጠኞች የደረሰባቸውን ሰቆቃ ሲናገሩ ስሜት በሚቆረቁር ሁኔታ ስለነበር አዳራሹ ውስጥ የነበሩት ሁሉ በሃዘን ተውጠው ነበር ተብሎአል። በተለይ ጋዜጠኛ ማርቲን ሽበየ በወቅቱ የደረሰባቸውን ጭካኔ የተሞላበት ድርጊት ሲናገር በሃሰት የተቀነባበረባቸውን ውንጀላ በማስረጃ ለማስደገፍ ሲሉ የፈጠሩትን የውሸት ፊልም ለመቅረጽ በረሃ ውስጥ ብዙ ቀናት እንዳቆዩቸውና መንገላታት እንደደረሰባቸው በመጨረሻም ያንን ፊልም ለፍርድ በየት እንደማስረጃ እነደተጠቀሙበት አስረድቶ ፊልሙን ለመቀረጽ ፈቃደኛ የሆንነው ህይወታችንን ለማቆየት ስንል ነው በማለት በምን አይነት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንዳለፉ ሲቃ እየተናነቀው ገልጾአል። ጋዜጠኛ ማርቲን አሳሪዎቻቸው የኦጋዴን ብሄራዊ ነጻነት ንቅናቄን ONLFን እነዲናወግዝላቸው ተጠይቀን ፈቃደኛ ሳንሆን ቀርተናል ብሎአል።

ፍትህ በሌለበት ፍርድ ቤት ከቀረቡ ቦኋላ የአሥራ አንድ አመት እስራት ተፈርዶባቸው ቃሊቲ ወህኒ ከወረዱ ቦሃላ በአንድ ክፍል ውስጥ እስከ 250 ዕስረኞች ታጉረው እንደሚገኙ፤ በእስር ቤት ቆይታቸው የተለያዩ ሰዎች እንደሚገረፉ ያውቁ እንደነበር የመሰከሩ ሲሆን ሃሳብን መግለጽ እንሸብርተኝነት የሚቆጠርበት አገር ውስጥ በሰዎች ላይ የሚፈጸመው ሰቆቃ ምን ያህል አስከፊ እንደሆነ የአይን ምስክር ለመሆን በመብቃታቸው ይህ እንዲቆም ከአሁን ቦኋላ ተግተው ለመታገል የሚችሉበትን ወኔና ድፍረት ሰንገው እንደወጡ ገልጸዋል።

በመጨረሻም በአሁኑ ሰዓት በቃሊቲ እስር ቤት ታጉረው የሚገኙ በርካታ እስረኞች በተፈታንበት ወቅት እየደረሰባቸው ያለውን ግፍና መከራ ለአለም ህዝብ እንድናሳውቅላቸው አደራ ስላሉን በቅርቡ በምናሳትመው መጽሃፍ ዝርዝሩን ይፋ እናደጋለን በማለት ቃል ገብተዋል።

ጋዜጠኞቹ ከእስር ለመፈታት ጽፈው አስገብተዋል ስለተባለው የይቅርታ ደብዳቤ ጉዳይ ተጥይቀው በሰጡት ምላሽ ምንም ወንጀል ሳንፈጽም በሃሰት በተቀነባበረብን ክስ የአስራ አንድ አመት እስራት ስለተፈረደብን ለመገላገል ስንል ያደረግነው ነው በማለት ወያኔ በሃሰት ወንጅሎ ይቅርታ በማስጠየቅ የሚመጻደቅበትን የጅሎች ጥበብ እርቃኑን አውጥተዋል።

ሁለቱ ጋዜጠኞች የሰጡትን ጋዜጣዊ መግለጫ በርካታ ኢትዮጵያዊያን አዳራሽ ውስጥ ገብተው እንደተከታተሉና የወያኔን አምባገነንነት በማጋለጥ ላሳዩት ጀግንነት ምስጋናቸውን እንዳቀረቡላቸው ተያይዞ የደርሰን ዜና ያስረዳል።

አድማጮቻችን በሲውድንኛ ቋንቋ የተሰጠውን የሁለቱ ጋዜጠኞች መግለጫ ሙሉ ትርጉም ጊዜ ካገኘን ወደፊት ይዘን የምንቀርብ መሆናችንን ከወዲሁ እንገልጻለን።

## የቀድሞ የህወሃት አመራር አባላት ወደሥልጣን ለመመለስ ከፍተኛ ተጋድሎ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ውስጥ ያሉትን የቀድሞ ጓዶቻቸውን ድጋፍ በመያዝ አስቸኳይ የድርጅቱ ጉባዔ እንዲጠራና አሁን አመራር ላይ ያሉ በሙሉ ተሸረው አዲስ ምርጫ እንዲደረግ አስወስነዋል ተብሎአል። በህወሃት ውስጥ የተላለፈው ይህ ውሳኔ ወደ ኢህአደግ ምክር ቤትም ተገፍቶ አዲስ የአመራር ምርጫ ከ6 ወር ቦኋላ እንዲደረግ እስከዚያው በጊዜያዊነት የሚመረጡ የግንባሩ ሊቀመንበርና ምክትል ሊቀመንበር አገሪቱን በጋራ እንዲያስተዳድሩ እየጣሩ ነው ተብሎአል። በውሳኔው መሰረት የኢህ አደግ ምክር ቤት የሁለት ቀን ስብሰባ ተቀምጦ ለስድስት ወር ግንባሩን የሚመራ ሊቀመንበርና ምክትል ሊቀመንበር ለመምረጥ በትናትናው ዕለት መስከረም 4 ቀን 2005 ስብሰባውን ጀምሮአል። ስብሰባው በተያዘለት ፕሮግራም የሚጠናቀቅ ከሆነ በዛሬው ዕለት ማምሻው ላይ የደረሰበትን ውሳኔ ይፋ ያደርጋል ተብሎ ይጠበቃል።

---

## እኛ ህዝብ ስንል እና እነርሱ ህዝብ ሲሉ

በዓለማችን ላይ በህዝብ ስም ብዙ ክፉ እና ደግ ነገሮች ተሰርተው አይተናል። ሂትለር "እኛ ብቻ ወርቆች" ብሎ እርሱ ወርቅ ብሎ በሚጠራው ህዝብ ስም የሠራውን ሠርቶ አልፏል። በሌላ በኩል ማርቲን ሉተር ኪንግ ደግሞ ዘረኝነት የፈጠረውን ክፉ አስተሳሰብ ለመግደል ሲታገል ቆይቶ የመጨረሻውን መስዋእትነት ከፍሎ በክብር አልፏል።

ወዲህ ወደ አገራችን ስንመለስ ድምጻቸውን በጣም ከፍ አድርገው በህዝብ ስም የተገዘቱና የማሉ ገዥዎችን እናገኛለን።እጅግ በጣም ድምጹን ከፍ አድርጎ በተለየ መልኩ በህዝብ ስም የጮኸ ግን እንደ ህወሃት ያለ አልታየም። የጨኸቱን ያክል ደግሞ ህዝብን ያዋረድና ያንገላታት እንደ ህወሃት ያለም አልታየም። ከህወሃት በፊት የነበሩ አምባገነኖች ኢትዮጵያዊያን ሁነው ኢትዮጵያዊያንን የበደሉ ቢሆንም ህወሃት ግን ኢትዮጵያዊነት መንፍስ ሳይኖረው ኢትዮጵያዊያንን የበደለ ዘረኛ ድርጅት ነው።ከህወሃት በፊት የነበሩት ደርጎች ዘረኝነትን በቃልም በገቢሪም ሲገልጡ አልታዩም ህወሃት ግን ዘረኝነትን በቃልም በገቢሪም የገለጠ ድርጅት ነው።የዚህ ቡድን መሪ የነበረው መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያ "መሪ" እኔ ነኝ ብሎ ሲያበቃ ህዝቡን ለሁለት ከፍሎ ተወለድኩበት የሚለውን ብሄር ለይቶ "ወርቅ" ብሎ መጥራቱ የሰውየውን ማን መሆን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ዓብይ ጉዳይ ሁኖ ይቆያል። ከዚህ ቀደም የነበሩ ገዥዎች "እንኳንም ከኢትዮጵያ ተወለድኩ" ይላሉ እንጂ ደምና አጥንታቸውን ቆጥረው ወደ መንደራቸው ወርደው "እንኳን ወርቅ ከሆነው ብሄር ተወለድኩ" ሲሉ አልተሰሙም።

ከህወሃት በፊት የነበሩ ገዥዎች ግዜውና ሁኔታው በፈቀደላቸው መጠን አስበው የራሳቸውን ትልቅ ኢትዮጵያ ለመፍጠር ሲሉ ህዝቡን በደሉት እንጂ እንደ ህወሃት ወሰን በሌለው ዝሪፊያ ውስጥ አልተዘፈቁም። ህወሃት ተብሎ የሚታወቀው ድርጅትና አባላቱ ግን የባእድ አገር የያዙ ይመስል እጅግ አሳፋሪ በሆነ ዝሪፊያ ውስጥ ስለመዘፈቃቸው ብዙ ማስረጃዎችን አቅርቦ ማሳየት ይቻላል። ህወሃት ለህዝብ ቆሜያለሁ እያለ ያንኑ ህዝብ ለመዘረፍ የዘረጋው የዝሪፊያ መረብ በየትኛውም አገር ታሪክ ታይቶ የሚያወቅ አይደለም። በመንግስት ስም ተደራጅቶ የገዛ አገሩን የዘርፈ፤የገዛ አገሩን ጥቅም ለባእድ አሳልፎ የሰጠ ቡድን እንደ ህወሃት ያለ በአገራችን ታሪክ አልታየም። አልተሰማም። ባለፉት ሃያ አንድ ዓመታት ጉዞ ውስጥ ህወሃት የተባለው ዘረኛ ቡድን ለህዝብ ቆሜያለው የሚለው ውሸቱን መሆኑን በተግባር አሳይቶናል።ለህዝብ የቆመ ቡድን ከገዛ አገሩ በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር ዘርፎ በባእዳን አገር አይደብቅም። ለህዝብ የቆመ ቡድን ከህዝብ የሚሠውረው ምንም ነገር አይኖረውም። ለህዝብ ቆሜያለው የሚል ቡድን ዛሬ የተናገረውን ነገ እያፈረሰው በአገር እና በህዝብ ላይ የወንበዴ ጨዋታ አይጫወትም።

ቀደም ብለው የነበሩ አምባገነኖች ያሉትን የሚያደርጉ በቃላቸው የሚገኙ ሲሆኑ ህወሃት ግን በቃሉ የማይገኝ ውሸትን ባህሉ አድርጎ የተቀበለ ድርጅት ነው። የቀድሞው ገዥዎች እኛ ዲሞክራት ነን ውጡና የመሠላቸሁን ፓሪት አቋቁሙ፤ምርጫም አካሂዱ፤ ጋዜጣም ፃፉ ብለው ሲያበቁ ዞር ብለው ደግሞ በዚሁ ምክንያት የፓሪት መሪዎችን አላሳሩም፤ መራጮችን አልገደሉም፤ ጋዜጠኞቹን አላሳደዱም። የቀድሞው ገዥዎች ፓሪትም ምርጫም ጋዜጣም የለም ብለው እንቅጩን ነግረውን ሲያበቁ በዚያው ፀንተዋል።ህወሃት ግን የዴሞክራሲን ዋጋ ሳያውቅ ስለደሞክራሲ የጮኸ ግን ደግሞ ከሁሉም የከፋ እኩይ አምባገነንና አፋኝ ቡድን ሆኖ የህዝቡን መከራ አብዝቶ ሃያ አንድ ዓመት ዘልቋል።

ይሄው ድርጅት ህዝብ የሚለው አንድም ራሱን ሲሆን አንድም ደግሞ ስብእናቸውን በምስር ወጥ የገዛቸውንና በራሱ አምሳያ ጠፍጥፎ የሠራቸውን የግለሰቦችን ስብስብ ነው። የለም እኛ እውነት የሌለበት ሠፈራችን አይደለም ስብእናችንንም ለከንቱ ነገር አሳልፈን አንሰጥም ያሉ ሰዎች ግን ለህወሃት ህዝብም ሰውም አይባሉም።እንዲህ ያሉት የሰው ልጆች እንደጠላት ተቆጥረው የመከራ እንጀራን እንዲበሉ የመከራ ጽዋንም እንዲጎነጩ ወደ ዘብጥያ ተጥለው ብልቶቻቸወን ተቀጥቅጠው ዘር እንዳይተኩ መደረጉን በዓይናችን አይተናል በጆሯችንም ሰምተናል። አገሪቷ ሰው አልባ እስክትሆንም ድረስ ህወሃቶች የመዘዙትን ሰይፍ ወደ ሰገባው ላለመለስ እጃቸውን በደም ወጪት ውስጥ ነክረው ተማምለው ቁመዋል። እነዚህ ቡድኖች ሰውም ህዝብም የሚሉት ስብእናቸውን በልፋጭ ሥጋ የገዟቸውን አልባሌ ግለሰቦችን እንጂ ለስብእናቸው ክብር ሰጥተው የለም "እኔ ሰው" ነኝ ብለው ከሃሰተኞችና ከነፍሰ ገዳዮች ጋር አንተባበርም ያሉትን አይደለም።የወሃት ህዝብና የእኛ ህዝብ በጣም ልዩነት አሏቸው።

እኛ ህዝብ የምንለው ጣኦቱ መለስ ዜናዊ ለደጅ ጥናትም ለሌላም ወደ ውጭ አገር ይሄዳል በተባለ ግዜ እርሱ በሚያልፍበት መንገድ ላይ የእለት ተግባሩን ለማከናወን ተፍ ተፍ ሲል ተገኝቶ እየተገፈተረ ወደ ጉድጓድም ወደ ጓዳም ገብቶ እንዲደበቅ የሚደረገው ያንን በእግሩ የሚኳትነውን ዜጋ ነው ህዝብ ብለን የምንጠራው። ህወሃቶች ግን ህዝብ ብለው የሚጠሩት ጣኦቱን አጅበው ሰፈሩንና መንደሩን አስወጥረው የሚያስጨንቁትን እነዚያ ጥቂቶችንና ከእነርሱ ጋር ለሆዳቸው ሲሉ ብቻ የተሳሰሩትን እንጂ ተገፈታትረው ወደ ጉድጓድም ወደ ጓዳም የሚወረወሩትን ብዙሃኑን አይደለም። መለስ በዚህ ያልፋል በተባለ ግዜ ስንቱ ጉሽማ ደርሶበታል፤ ስንቱ ከቀጠሮው ዘይግቷል፤ ስንቱስ በማይፈልገው ቤት ውስጥ ገብቶ እንዲደበቅ ተደርጓል። ግን ለምን መለስ ያልፍበታል በተባለ መንገድ ላይ የተገኘ ሁሉ እየተገፈተረ ገደል ይጨመራል ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው መልስ ህወሃቶች በህዝብ ስም ድምጻቸው ከፍ አድርገው ባዶ ጩኸት የሚጮሁ ግን ደግሞ ያንኑ ህዝብ የማያምኑ ቡድኖች በመሆናቸው ነው። መተማመን ከበጎ ሥራ የሚመነጭ ነው። ህወሃቶች በጎ ሥራ የሌላቸው መሆናቸውን ስለሚያውቁት ሠርቶ አደሩን ህዝብ አያምኑትም። ይህ ሠርቶ አደር ህዝብ የራሱን ማህበር አቋቁሞ የራሱን መሪ እንዲመርጥም አይፈቅዱም። ሌላ ምንም ዓይነት አማራጭ እንዳይኖረውም አግደውታል። እኛ ህዝብ የምንለው ይሄን ነጻነቱን የተነፈገውን ነው።

እኛ ህዝብ የምንለው በኢቲቪና በበረከት ስምኦን ፕሮፖጋንዳ ተወጥሮ "ዲፐረስድ" የሆነውን ህዝብ እንጂ እነዚያ እነበረከት ስምዖንን ለመምሰል የሚኳትኑ ዘባተሎዎችን አይደለም።ዛሬ ጎሬቤታችን ኬኒያ ከአስር በላይ የግል ቴሌቭዥን ጣቢያ አላት።ህዝቧም የፈለገውን ቻናል እየመረጠ ያያል ይሰማል። ይሄ በኢትዮጵያችን የተከለከለ ነው።ለምን ቢሉ ነጻ ሚዲያ ካለ ዘረኛው ህወሃት እስከ ዛሬ በህዝብ ሥም የፈጸመው ወንጀል ተነግሮ እውነተኛ ማንነቱ እንዳይገለጥ ስለሚፈራ ብቻ ነው።እንግዲህ እነርሱ ህዝብ ብለው የሚጠሩት ከ30 ዓመት በላይ ወንጀል ሲፈጽም የኖረውንና ለዚህ ወንጀላቸውም መከደን የሚተባበሩትን እንጂ ለእውነት የቆሙትንና እውነቱ ይገለጥ የሚሉትን አይደለም።

እኛ ህዝብ ብለን የምንጠራውም የምንታገልለትም እንደ ጎሬቤቱ ኬኒያ አማራጭ ሳይኖረው በአንድ ቴሌቭዥን ብቻ በህወሃት ፕሮፖጋንዳ "ዲፕሬስድ" ሁኖ የሚኖረውን ብዙሃኑን ኢትዮጵያዊ ነው እንጂ የዜጎችን መረጃ የማግኘት መብት የነፈጉትን እና ለዚያ ተባባሪ የሆኑ ጥቂቶችን አይደለም።ባጠቃላይ ህወሃት/ ኢሕአዴግ ሕዝብ ብሎ የሚጠራውና እኛ ህዝብ ብለን የምንጠራው በእጅጉ ይለያያል። እነርሱ ህዝብ የሚሉት ራሳቸውን እና ራሳቸውን ብቻ ነው።ከእነርሱ ውጪ ያለ ለህወሃት ሰውም ህዝብም አይባልም።

በመጨረሻም ህዝብ ጥቂት የመሰብሰብ እድል ባገኘ ጊዜ "ሳንፈልጋቸው ሃያ ዓመታቸው" ብሎ የሚፈልገውን ተናግሯል።አዎን ሳንፈልጋቸው ሃያ አንድ ዓመት ዘር እየቆጠሩ ዜጎችን ያሰቃዩ እነዚህ ዘረኞች ከህግ በታች እስኪሆኑ ድረስ የተጀመረው ትግል በሁሉም ዘርፍ ተጠናክሮ ይቀጥላል። በኢትዮጵያችን ፍትህ እስከሚነግስ ድረስ፤ ነጻነት ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ እስከሚናኝ ድረስ፤ እኩልነት የአገራችን ዋና መገለጫ እስከሚሆን ድረስ፤ የተደበቀው ተገልጦ እውነቱ እስከሚነገር ድረስ፤በህወሃት የተዘራው የጥላቻ ዘር ከሥሩ ተነቅሎ በምትኩ ፍቅር እና አንድነት እስኪያብብ ድረስ የጀመርነውን ትግል አናቆምም።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## የዘረኛው አገዛዝ ቁንጮ የነበረው መለስ ዜናዊ በሞት ቢለይም . . . (ከገፅ 4 የዞረ)

ለመጡት የትግራይ ተወላጆች አብላጫውን ከፍተኛ ወታደራዊ ሹመት ማሰጠታቸው ኢህአደግ የገባበትን ውዝግብ እንደሚያባብሰው ተገምቶአል።

በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ ያሉት የሌላ ብሄረሰብ አባላት ይህንን አድሎአዊ የሹመት አሰጣጥ በፍጹም እንደማይቀበሉትና ቀደም ሲል በሰራዊቱ ውስጥ የነበረውን ዘረኝነት ውስጥ ለውስጥ ሲቃወሙ ለነበሩት የበታች መኮንኖችና ወታደሮች መጠናከር አስተዋጽ እንደሚያደርግ ተያይዞ የደረሰን መረጃ አመልክቶአል። የትግራይ ተወላጆች በሰራዊቱ አዛዥነት ቦታዎች ባላቸው የበላይነት ምክንያት መለያቸው "እሱ እኮ ህወሃት ነው፣እገሌ ብአዴን ነው..." መባባሉ አሁንም እንደቀጠለ መሆኑ ይነገራል።

መለስ ዜናዊ በህይወት በነበረበት ወቅት በጀኔቭ ዓለማቀፍ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ስብሰባ ላይ የአሜሪካ መንግስት ልዩ መልእክተኛ የሆኑት አምባሳደር ዳግላስ ህወሃት በመከላኪያ ሠራዊት አዛዥነት ቦታ ያለውን አብላጫነት አደባባይ ላይ በማውገዛቸው ኢዲየት" ብሎ ሰድቦአቸው እንደነበረ ይታወሳል።

የመለስ ዜናዊን ሞት ተከትሎ በአገሪቱ ውስጥ ለ21 አመታት ተንሰራፍቶ የኖረው ዘረኛ መዋቅርና አሰራር ሊሻሻል ይችላል ተብሎ በአንዳንድ ምዕራባዊያን ሊጋሾች ዘንድ ሲጠበቅ ወደ ሥልጣን እየመጣ ያለው አዲስ ቡድን የነበረውን ዘረኛነት የሚያጠናክር ሹመት መስጠቱ አሳፋሪና አስደንጋጭ ሆኗል የሚሉ አስተያየቶች በመደመጥ ላይ ናቸው።

## ህወሃት መለስ ዜናዊን ለመተካት ሰሞኑን አድርጎት በነበረው ዝግ ስብሰባ አባይ ወልዱን የድርጅቱ ጊዜያዊ ሊቀመንበር አድርጎ መሾሙ ተዘገበ

የህወሃት ሥራ አስፈጻሚ ሰሞኑን ባካሄደው ስብሰባ በሟቹ መለስ ምትክ በአሁኑ ወቅት የትግራይ ክልል ፕሬዚዳንት ሆኖ በመስራት ላይ የሚገኘውን የፓርቲው ምክትል ሊቀመንበር አባይ ወልዱን ሊቀመንበር አድርጎ ሲመርጥ ኦህዴድ በበኩሉ ከህመም ጋር በተያያዘ የመልቀቂያ ደብዳቤ አስገብቶ በነበረው አለማየሁ አቶምሳ ምትክ ወያኔ የአ/አ ከተማ ከንቲባ አድርጎ የሾመው ኩማ ደመቅሳን በሊቀመንበርነት መምረጡን ምንጫች አረጋግጠዋል።

እንደምንጮቻችን መረጃ አዳዲስ ሊቀመንበሮቹን የሾመው የኢሃደግ አባል ድርጅቶች አመራር ኃይለማርያም ደሳለኝን ጠ/ሚኒስትር፣ ኩማ ደመቅሳን ደግሞ ምክትል ጠቅላይ ምንስቴር በማድረግ ከስድስት ወራት ቦኋላ ይደረጋል የተባለው የግንባሩ ጉባዔ እስኪካሄድ ድረስ በጊዜያዊነት እንደሚሾም ይጠበቃል፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ ሰሞኑን የአውራምባ ታይምስ በድረገጹ ይፋ ባደረገው ዘገባ፤ ሀይለማርያም ደሳለኝን በጠቅላይ ሚኒስትርነት ከማስቀጠል ውጪ ሌላ አማራጭ ያጣው ኢህአዴግ፤ በሀይለማርያም አመራር ላይ እምነት ስለሌለው በሥሩ ሦስት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮችን ለመሾም እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ገልጾአል።

ሪፖርተር የተባለው የወያኔ ጋዜጣ በበኩሉ በጠቅላይ ሚኒስትርነት ይመረጣል ተብሎ የሚጠበቀው ሀይለማርያም ደሳለኝ የቀድሞ አለቃው መለስ ዜናዊን ያህል አቅም ስለማይኖረው፤ ኢህአዴግ ከአንድ በላይ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮችን ሊሾምለት እንደሚችል በትናትናው ዘግባው ይፋ አድርጎአል።

ለስደት በተዳረገው የቀድሞው አውራምባ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ዳዊት ከበደ የሚዘጋጀው አውራምባ ታየምስ ይፋ እንዳደረገው ፤ሦስቱ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮች፤ አንዱ ከኦሮሞ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ድርጅት(ኦህዴድ)፣አንድ ከብሔረ-አማራ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ(ብአዴን) እና አንድ ከሕዝባዊ ወያነሀርነት ትግራይ(ህወሀት) የተውጣጡ ይሆናሉ።

ከኦህዴድ ለምክትል ጠቅላይ ሚንስቴርነት የታጨው ግርማ ብሩ ሲሆን እሱም የኢኮኖሚ ጉዳዮችን የሚመሩ ዘርፎችን በሙሉ ይመራል ተብሎአል። ብአዴንን ወክሎ ደግሞ የወያኔ ትምህርት ሚንስተር ሆኖ በመስራት ላይ ያለው ደመቀ መኮንን የማህበራዊ ዘርፎችን የሚመራ ምክትል ጠቅላይ ምንስቴር ሊሆን እ ንደሚችልና ሦስተኛውና ከህወሀት የሚሾመው ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር የውጪ ጉዳይና የመከላከያና ደህንነት ጉዳዮችን አጠቃሎ እንደሚይዝ ተዘግቦአል።

ይህ በዚህ እንዳለ ከሦስት ወር በላይ በእርስ በርስ የስልጣን ሽኩቻ ዉስጥ ተዘፍቆ ኢትዮጵያን ካለመሪ ያስቀራት የወያኔ አመራር የሚቀጥለዉን የአገሪቱን መሪ በመተካቱ ሀደት ላይ ከስምምነት ላይ መድረስ ባለመቻሉ አትዮጵያ ለሚቀጥሉት ስድስት ወራት በጠ/ሚኒስትርና በምክትል ጠ/ሚኒስትር የጋራ አመራር እንደምትመራ የኢህአዴግ ጽ/ቤት ኃላፊ የሆነዉ ሬድዋን ሁሴን ከትናትን በስቲያ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ በሰጠዉ ቃለመጠይቅ አስታውቆአል።

እንደሬዲዋን ሁሴን መግለጫ የኢህአዴግ ምክር ቤት በያዝነዉ መስከረም ወር አጋማሽ በሚያካሄደዉ ስብሰባ ላይ የሚመርጣቸዉ የግንባሩ ሊ/መንበርና ምክትል ሊ/መንበር ግንባሩን ለስድስት ወራት ብቻ በጋራ ይመሩታል።

የግንባሩ የሚቀጥለዉ ጉባዔ ከስድስት ወራት በኃላ እንደሚካሄድ የተናገረዉ ሬድዋን ሁሴን ይህ አስከሚሆን ድረስ ግን ከአራቱ የግንባሩ አባል ድርጅቶች የተዉጣጡ 180 አባላት የተወከሉበት የግንባሩ ም/ቤት በተጓደሉት አባላት ምትክ ግንባሩን "በጋራ የሚመሩ" ሊቀመንበር እና ምክትል ሊቀመንበር ይመርጣል ብሏል፡፡ ከስድስት ወራት በኃላ በሚካሄደዉ የግንባሩ ጉባዔ ላይ ግን ሊቀመንበሩንና ምክትል ሊቀመንበሩን ጨምሮ የሥራ አስፈጻሚና የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላትም ከቦታቸዉ ተነስተዉ ሌላ አዲስ ምርጫ እንደሚካሄድ ሬድዋን ሁሴን በቃለ ምልልሱ ወቅት ተናግሯል።

ኢህአዴግ ከተመሰረተ ጀምሮ የተከተለዉን አሰራር ለምን መቀየር እንዳስፈለገዉና ለምንስ በመለስ ዜናዊ ምትክ ሌላ ጠ/ሚኒስትር መምረጥ እንዳቃተዉ ሬድዋን ሁሴን መናገር ባይፈልግም ጉዳዩ ያለመግባባትና የሽኩቻ ምልክት ነዉ ሲሉ ብዙ የፖለቲካ ጠበብቶች ይተቻሉ።

የኢሃደግ ጽ/ቤት ሃላፊ ሬድዋን ሁሴን በአድስ ዘመን ጋዜጣ ከሰጠው መግለጫ ጋር የሚጣለዝ መረጃ በየቀኑ እየወጣ መሆኑ የሚያመለክተው ህወሃት እንዳሻው በሚያሽከረክረው ግንባር ውስጥ ያሉ ግለሰቦች የሚሰጡት መግለጫ ምንጊዜም ሊቀየር ስለሚችል ታዓማንነት እንደሌለው ይታወቃል። የሚንስቴሮች ምክር ቤት የተባለው ስብስብ ስለ ሃይለማሪያም ደሳለኝ ሹመት በቅርቡ የሰጠው መግለጫና እስከዛሬ ተግባራዊ ያለተደረገው ውሳኔ ይህንን ሃቅ እንደሚያረጋግጥ ግልጽ ሆኖአል።

## የዘረኛው አገዛዝ ቁንጮ የነበረው መለስ ዜናዊ በሞት ቢለይም

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

1. ብርጋዴር ጀነራል ያይኔ ስዩም ገብረማሪያም – ብሔር ትግሬ
2. ብርጋዴር ጀነራል ጉዕሽ ፅጌ ወልደገብርኤል – ብሔር ትግሬ
3. ብርጋዴር ጀነራል ደግፌ ቢዲ ደጊዮ – ብሔር ትግሬ ፡፡
4. ብርጋዴር ጀነራል ገብሩ ገብረማሪያም ወልዱ – ብሔር ትግሬ
5. ብርጋዴር ጀነራል ወልደ ገብርኤል ባቢ ገብረመድህን – ብሔር ትግሬ
6. ብርጋዴር ጀነራል ፍሰሃ ኪዳነ ማሪያም ወልደህይወት – ብሔር ትግሬ
7. ብርጋዴር ጀነራል ሀለፎም እጅጉ ሞገስ – ብሔር ትግሬ
8. ብርጋዴር ጀነራል አታክልቲ በርሄ ገብረማሪያም – ብሔር ትግሬ
9. ብርጋዴር ጀነራል አብረሃ አረጋይ ለገሰ – ብሔር ትግሬ
10. ብርጋዴር ጀነራል ማዕሾ ሃጎስ ስዩም – ብሔር ትግሬ
11. ብርጋዴር ጀነራል ገብረመድህን ፍቃዱ ሃይሉ – ብሔር ትግሬ
12. ብርጋዴር ጀነራል ፍስሃ በየነ ስዩም – ብሔር ትግሬ
13. ብርጋዴር ጀነራል ገብረኪዳን ገብረማሪያም የአቢዩ – ብሔር ትግሬ
14. ብርጋዴር ጀነራል ጥጋቡ ይልማ ወንድም ሁነኝ – ብሔር ትግሬ
15. ብርጋዴር ጀነራል አስራት ዶነሄሮ አህመድ – ብሔር ቅይጥ
16. ብርጋዴር ጀነራል መሾሻ ገብረሚካኤል ኪዳነማሪያም – ብሔር ትግሬ
17. ብርጋዴር ጀነራል አብርሃ ተስፋዬ ብረሄ – ብሔር ትግሬ
18. ብርጋዴር ጀነራል አስካለ ብርሃን ተራ – ብሔር ትግሬ
19. ብርጋዴር ጀነራል የማነ ሙሉ ሃብተ – ብሔር ትግሬ
20. ብርጋዴር ጀነራል ሙሉ ግርማይ ገብረህይወት – ብሔር ትግሬ
21. ብርጋዴር ጀነራል ዘውዱ በላይ ማለፊያ – ብሔር ትግሬ
22. ብርጋዲየር ጀነራል ይብራህ ዘሪሁን አድጎ – ብሄር ትግሬ
23. ብርጋዴር ጀነራል አሰፋ ገብሩ ወርቅነህ – ብሔር ትግሬ
24. ብርጋዴር ጀነራል ካሳሁን ታረቀኝ ብሩ – አማራ
25. ብርጋዴር ጀነራል ይመር መኮንን አሊ – አማራ
26. ብርጋዴር ጀነራል አቤል አየለ አልቶ – አማራ
27. ብርጋዴር ጀነራል ከድር ይበርሳ ይመር – ኦሮሞ
28. ብርጋዴር ጀነራል ድሪባ መኮንን ሃትሆ – ኦሮሞ
29. ብርጋዴር ጀነራል ሹማ አብደታ ሂካ – ኦሮሞ
30. ብርጋዴር ጀነራል ደስታ አብቺ አገኖ – ኦሮሞ
31. ብርጋዴር ጀነራል ዱባለ አብዲ ሁሉቃ – ኦሮሞ
32. ብርጋዴር ጀነራል ኩመራ ነገሪ ገመዳ – ኦሮሞ
33. ብርጋዴር ጀነራል ኩምሳ ሻንቆ ደስታ – ደቡብ ህዝቦች
34. ብርጋዴር ጀነራል አጫሉ ሸለመ መርጋ – ደቡብ ህዝቦች ናቸው

**ከብርጋዲየር ጀነራልነት ወደ ሜጀር ጀነራልነት ያደጉት ሦስቱ ደግሞ ፡-**

1. ሜጀር ጀነራል መሰለ በለጠ አለሙ – ብሔር ትግሬ
2. ሜጀር ጀነራል መሐሪ ዘውዴ ገብረማሪያም – ብሔር ትግሬ እና
3. ሜጀር ጀነራል ሐሰን ኢብራሂም ሙሳ – ብሔር ትግሬ ናቸው።

እንደ ውስጥ አዋቂ ምንጮቻችን ይህ ባለፈው ማክሰኞ መስከረም አንድ ቀን ሁለት ሺ አምስት ለቀድሞ የህወሃት ተጋዳላዮች የተሰጠው ወታደራዊ ሹመት የመለስ ዜናዊን ሞት ተከትሎ ድርጅቱ ውስጥ በተፈጠረው የሥልጣን ክፍተት ወያኔ በመከላኪያና ደህንነት አዛዥነት ቦታ ላይ ያለውን ይዞታ በማጠናከር የአገዛዙን ዕድሜ ለማራዘም እያደረገ ያለው ጥረት አካል ነው ተብሎአል።

በረከት ስሞኦን ዋና ተዋናይ ሆኖ በሚንስቴሮች ምክር ቤት ውስጥ ብአዴንና ኦህደድ ያላቸውን አብላጫ ድምጽ በመጠቀም ሃይለማሪያም ደሳለኝን እስከሚቀጥለው የወያኔ ምርጫ ድረስ በሟቹ መለስ ዜናዊ ቦታ ተተክቶ በጠቅላይ ሚንስቴርነት እንዲሰየም ያስተላለፈው ውሳኔ የገለበጡት ህወሃቶች መሆናቸው በስፋት እየተነገረ ባለበት በአሁኑ ወቅት ፓርቲያቸውንና አገሪቱን የሚመራ ጠቅላይ ምንስቴር ማን መሆን እንዳለበት ከስምምነት(ወደ ገፅ 3 ዞሯል)

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org